# ለኢትዮጲያ ና ለህዝቧ የሚበጀው ነገር (ክፍል ፬ )

*ከሙሉቀን ገበየው*

በክፍል ፫ ጽሁፌ ያንሳሁት ሃሳብ በተለይ ሁሌም የምንሸሸውና የማንነጋግርበት፤ ነገር ግን ሊሁን የሚችል ትልቅ አደጋን መመልከት ነበር። ወያኔው ለ 27 አመት ባቀነቀነው ብልሹ ዘርን መሰርት ያደርገ ፖለቲካ ህዝቡ እክ እንትፍ ቢያደርገውም ስርአቱ ሙሉ ለሙሉ ስላልፈርሰና ከውስጡም በመጡ "የለውጥ ፈላጊዎች" ከነ እድፋቸው የሽግግሩን ሂደት በመሪንት በማያዛቸው፤ በተለይ ደግሞ የዘር ፖለቲካን የሚያቀነቀኑ ከወያኔው ጋ ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ነገር ግን ወያኔ ስልጣን ሳያጋራ ያባረራቸው የጎሳ አክራሪ የፖለቲካ ድሪቶ ፓርቲዎች ሀገር ቤት ከንግሳንግሳቸው ያለ ስርአተና ህግ እንዲገቡና እንድፈንጥዙ በመደርጋቸው እንዲህም በጥላቻና ልይኑት ላይ ያተኮረ ግማሽ እውነት ይዘው በተጋነነ ትርከት ህዝቡ ወስጥ ከነሚድያቸው እንዲገቡ ስለፈቀደና፤ ህዝቡንም በፕሮፓጋንዳ ሰመምን ውስጥ በማስገብታቸው፣ ዋና አልማቸው አድርገው የያዙትን ማስፈራርያ የመገንጠል ጥያቄን እውን ቢያደርጉትና ቢሆንስ እወንታው ምን ይሆን የሚለውን ነበር። ገንጥዬ ነጻ አገር አደርጋታለው የሚሉትን ስንመርመርው እንድሚያስቡት ማርና ወተት የሚፍስባት ሃገር ሳትሆን ወያንሌው በፈጠራላቸው የሃሰት ወሰንና ድንብር ምክንያት ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያምያቕርጥ ጦረነትና አሳትና ለቅሶ፣ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መግባትና የሶማሊያን፣ የሶርያን፣ የየመንን እንዲሁም የቀድሞ ዩጎዝላቪያን እጣ መጋራት እንድሚሆን፤ ዋና አቀንቃኞቹ ግን ህዝቡን ማግደው እነርሱ የያዙትን የአሜሪካ፣ የካናዳ የአውሮፓና አውስትርሊያ ፓስፖርታቸውን ይዘው እንደሚፈርጥጡ፤ ቢሳካልቸው በሃይማኖት እንዲሁም በአውርጃና በመንድር ነፃ አገር እንሁን ገደብ ድርስ እንድሚወርዱ ተብራርቶል። ያም ካልታሳካልቸው እንደ ወያኔው የራሳቸውን ጎሳ ስም በምጠቀም በሌሎች ላይ በበላይነት በመቀመጥ "ድርሻውና ግዜው የኛ ነው" የሚል ሌላ አገዛዝ ቀንበር ለመጣል ተዘጋጅተውና ስትራተጂ ነድፈው መምጣታቸው ተብራርቶል።

በዚህኛው የመጨረሻ ክፍል ጽሁፌ የምመለከትው ጉዳይ የለውጡ አራማጆች፣ "መሪዎች" እንዲሁም ህዝቡም በዚህ ሽግግር ወቅት ትኩርት እንዲሰጡባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ሲሆኑ ባጠቃላይ በ፫ ክፍል ላቀርብኩት ጽሁፉ ማጠቃልያና መድምድሚያ ነው።

አገራችን ኢትዮጲያ መስቀልኛ መንግድ ላይ እንድመሆኗ በሚቅጥሉት ወራቶች የሚወሰኑ ሃገራዊ ጉዳዮች እንደምታቸው ለርዥም ዘመን የሚሆን ስለሆነ ጥንቃቄና ማስትዋል ያለበት ትልቁን ሃገራዊ ሃሳብ ሰላምና አንድነት፣ የህዝብ መቀራረብን የአብሮ ማደግን፣ በተለይም ግፍና ጭቆናን የሚቀርፍና የዜግነት ሙብት የሚስምርበት ዲሞክራስያዊነትን መሰረት ያደርግ መሆን አለብት። አንጋፍው ፕሮፌሰር መስፍን ወልማርያም በመፀሃፋቸው እንዳሰፈሩት የኢትዮጲያ ህዝብ ያቄማል፣ ግዜ ጠብቆ መንግስትን ለማውርድ አብሮ ያግዝና አውርዶ ወደ ቤቱ ይመልሳል ነግር ግን ወድፊት የሚቀመውን መንግስት ግን አይሰራውም ያሉት ተደጋጋሚ የቅርብ ግዜ የታሪክ እውንታን ደግሞ እንዳይፈጸም ህዝቡም ለዘላቂ ለውጥ መንሳስትና የሚመጣውን የመንግስተ ስርአት በዘላቂነት በአዲስ መልክ ሰርቶ መሆን አለበት ቤቱ መግባት ያለበት።

በቅርቡ አንድ ታዋቂ ወጣት የፖለቲካ ሰው እንድተናግሩት ያአገራችን ና የህዝቡ ቀንበር ዋናው ችግሩ ባገዛዝም በተቃዋሚውም አመራር ያሉ የፖለትከኞች መጥፎ የፖለቲካ ልምድ ነው።የችግሩ አንዱ መፍቴህ መሪዎቹ፣ የፖልቲካ ፓርቲዎቹ ከህዝቡ ጥያቄና ፍላጎት ጋር ለመጣጣም፣ ለመለወጥ ዝግጁ መሆን አለባቸው። ይህ ትልቅ እውነት ያለው አነጋግር ነው። የመጥፎ እድል ጉዳይ ሆኖ አብዛኛው ፖለቲኮኞቻችን ወደ ፖለቲካው አለም ሲገቡ ለህብረትሰቡ የሚጠቅም ስራ ለምስራት አስበን ነው ሳይሆን እንዴት ጥቅም፣ ስልጣን፣ ሃይል፣ ሃብት፣ ታዋቂነት እንድሚያግኙ ዋናው አላምቸው አድርገው ነው። ይህንን እውንታ እንርሱ ቢክዱትም (at subconscious level that is the truth) ድርጊታቸው የሚያሳየው ግን ያንን ነው። እነርሱ ሳይለውጡ እንምራዋለን የሚሉትን ህዝብ ችግር እንዴት በዘላቂነት ሊለውጡ ይችላሉ?

ነገሮችን ከስር መስረቱ ቀለል ባለ መልክ እንመልከትው። በ ታሪክ አጋጣሚም ይሁን በእግዚሃቤር ፈቃድ አብዛኞቻችን ኢትዮጲያ ተፈጥረናል ወይም ተውልደናል። ባአለም ላይ ያሉ አብዝኞዎቹ ሃገራት ሁሉ አሁን ያሉበት የአገር ህዝብና ወሰን ላይ የደረሱት በተለያየ ግዜ የህዝብ ፍልሰትና በጦረነት ውጤት መሰረት ነው። ይሄ ነገር በኛ አገር ብቻ የሆነ አይደለም። የሰው ልጅ ከታሪክ ይማራል እንጂ የቀድመውን ታሪክን አሁን አይኖርውም። እኛም ይህን ማወቅ ይኖርብናል።የሰው ልጆች ማህበራሰባዊ ና ታሪካዊ እውንታዎች የሚያስየን በተለይ ባለፉት 50-100 አመታት ያይነው የተማርነው እውንታ፡ ሰዎች በመውያየት በመነጋገር የጋራ ሰላም፣ ብልጽግና እንዲሁም እድገት ሊይመጡ መቻላቸውን ነው። የአውሮፓ አገራት ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ናቸው። አንዱ ሌላውን ጨቁኖ ሊዘልቅ እንድማይቻል ከአለም እንዲሁም ከራሳችን የትግል ልምድም የምናውቀው ነው።

አሁን ያለንበት አገራችን ኢትዮጲያ የጋራ ቤታችን ናት። ለሁላችንም በእኩልነት ዜግነት ሊኖርን ይገባል። አንዱ ከሌላው የበለጠ ዜጋ ሊሆን አይችልም ወይም አይገባም። ይህም እንዲሆን መፍቀድ የለብንም። ይህን የጋራ ቤታችንን አውቀን፣ ተከባበርን ካልጠበቅናት ሌለ ሃይለኛ ሊወስዳት ይችላል። አባቶቻችን ካለም ሃገራት ሁሉ በተለየ ትልቅ ውልታ ያደርጉልን ይህችን ሃገር በጋራ ሁነው ሀይለኞች እንዳይውስዱብን አጥንቻቸውንና ደማቸውን አፍሰው ለኛ ያስርክቡን ታሪካዊ አገር ናት። እኛ ደግሞ ከነሱ የተሻለ የመንግስት ስርአትና መሰርተንና ሀገር ጠብቀን ለልጆቻችን ማስርከብ ግዴታ አለብን። ካለበልዚያ የተረከብነውን አደራ የማንውጣ በታሪክም በወድፊቱም ትውልድ ተወቃሾች እንሆናለን።

አገራችን ላንዱ እናት ለሌላው የእንጀራ እናት እንድትሆን ማደርግ የለበንም። ሁላችንም እኩል ልጆቹዋ የምንሆነው በዜግንታችን ላይ መሰረት ያደርገ መንግስት ስንመስርት ነው። በጎሳ፣ በሀይማኖትና በቋንቋ መሰርት አድርገን እርስ በርሳችንን መካከል አጥር ከሰራን ሃገራችን የጋር አገርና እኩል ልጆችዋ አንሆንም። እኩልንት የጎደልባቸው ወንድሞቻችን መብታቸውን ለማግኘት ይታገላሉ ፤ ይህም ሰላም ያደፈርሳል፣ በዚህም አገር ትደማልች ወገንም ይሰቃያል። ሌላው ቢቀር አባቶቻችን በመካከላቻው የነበርውን መጨቛቆን ወደ ጎን አድርገው ያስርከቡንንም አገር አፍርሰን ቤት አልባ ህዝብ እንሆናልን።

ታድያ መፍቴው ምንድን ነው?

ከዚህ ትንሽ ገለጻ የምንገነዘበው፣ በዜግንት ሁላችንም እኩል የሆንበት መንግስት መስርተን በመካክልችን ያለው የ ቋንቋ የባህል የወግ የመሳሰለውን ልዩንታችን ጌጥ አደርገን በመከባብር የጋር ማደርግ ስንችል ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ ዜጋ ነኝ ብሎ በኩራት የሚናገረውና ውስጡም የሚያምነው በየትም የአገራችን ክፍል ተዘዋውሮ ህብት አፍርቶ ህግ አክብሮ መኖር ሲችል ነው። ይህን ለማድርግ ደግሞ አሁን ያለንበት የሽግግር ግዜ በሚወሰኑ ታላላቅ ጅማሮወች የሚመስርት ይሆናል።

ቀደም ብዬ ባቀርባኳቸው ፅሁፎች ላይ እንዳብራራውት መድርግ ያለባቸውን አንኳር ጉዳዮች አቀርባለው። ሃስቦቹ ቀድምው የተብራሩ ስለሆነ ለማጠቃለል ያህል እንደ ቅድመ ተከተልቸው እንዲፈጸሙ እዘርዝራልሁ።

1. የሽግግሩ የለውጥ መሪዎች ከቀደመው ስርአት የመጡ "የለወጥ ፈላጊዎች" በመሆናቸው በሙሉ ሃይልና ፍላጎት ሽግግሩን ሊወጡት ብቻቸውን ስለማይቻላቸው የተለያዩ ነገር ግን አገርና ህዝብ አዳኝ አመለካከት ያላቸውን ያገር ሽማግሌዎችን፣ ሙሁራንን፣ የሞያ ማህበራትን ቢያካትትና ባገራችን ውስጥ ያሉ የፖልቲካ ድርጅቶችን ሁሉ የሚሰበስቡብት ምክር ቤትን እያማከረ የለውጡን ሂደት ማፈጠን።

2. ላልፉት 45-50 አመታት አሁን ባለው የአገራችን ህዝብ ላይ የተፈጸመን በደልና የክፋት ስራ በዳይና ተብዳይ ተግናኘተው (የፖልቲካ ድርጅቶችንም ጨምሮ) የይቅርታ፣የእርቅ የፍርድ በህዝብ መካከል የመግባቢያ ሰፊ መድርክ ተደርጎ (ከ ደቡብ አፍሪካ ልምድ መማር ይቻላል) ያለፈውን የክፋት የቂም በቀል የሃዝን ድባብ ዘግተን በአዲስ እህት-ወንድማምችነት በዳይና ተበዳይ ይቅር ተባብለው በሰላም የሚኖሩባት ሃገር መስርተ መጣል።

3. ሕዝባችን ለመከራና ለብዝበዛ የተጋረጠው ገዥዎች የተጠቀሙብትን የከፋፍልህ ግዛው የልዩንት መሳርያ የሆነውን ፖሊሲና ህግ አፍራሽ መሆኑን ትልቅ አጽኖት ተሰጥቶት፤ በህዝቡም ዘንድ በፖለቲካ ፓቲዎችም ዘንድ ያንን አስከፊ ባህል ተመልሶ እንዳይመጣ መስማማት።

4. ለወደፊት ትልቅ በሽታ የሚሆኑብንን የከፋፍልህ ግዛው ህጋዊ መሰረት የሆነውን ወያኔ ላገዛዙ ያምቸው ዘንድ በላይችን ላይ የጫነውን ህግ-መንግስት መመርመር፣ ካስሰፈለገንም የልዩንታችን የሚያስፋ መሰርት የሆኑትን ህጎች ማውጣት ወይም ህዝብ ሁሉ የሚመክርበት አዲስ ህገ-መንግስት ማጽደቅ።

5. በዘር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ፓርቲ አገር አፍርሽና ህዝብ ረባሽ ስለሆነ ህዝቡንና የፖለቲክ ፓርቲዎችን አነጋግሮ ተምክሮ ተስማምቶ በዘር ላይ ወይም ጎሳ ላይ የተመሰርተ የፖለቲካ ድርጅትን በህግ ማገድ።

6. በመንግስት መንበር ላይ የተቀመጡት ሃላፊዎች የአገርና የህዝብ ሰላምን፣ የደህነንትን ህግ ማስከበር ግዴታቸውን እንዲውጡ መስራት አለበት። ህግ ወጥ ሀይለኞችን፣ ከህግ ውጪ መሳሪይ ታጥቀው

ህዝቡን የሚያስፍራሩ ወንጀለኞችን ስብስብ እንዲሁም በማን አለበኝነት ባደባብይ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ፣ ለጦርነት የሚያንሳሳ ፕሮፖጋንዳን የሚነዙ ግልሰቦችን ወይም ስብሰቦችን እንዲሁም ሚዲያ ተቋማትን በህግ ጥላ ስር ማድርግ።

7. የአገር ሰላምን የህዝብ ደህንንትና ጸጥታን የማያወክ ነገር ግን የተለያይ ሃሳቦችና አመለካከቶችን የሚቀርቡብትን ነጻ ሚዲያን ህትመትን መፍቀድ ማበራታት።

8. በሽግግር ላይ ያለው የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግስታት ስልጣን ላይ የተቀመጡት በትክክልኛ የህዝብ ድምጽ ተምርጠው ሳይሆን ገዠው ወያኔ ይመራው የነበረው መንግስት ሁሉን አግልሎ፣ ራሱን ብቻ አስቀምጦ በማስፈራርት በተደርገ የሃሰት ምርጫ መሆኑን አምነው፤ እውንትኛው የህዝብ ምርጫ እስኪምጣ ድርስ ሽግግሩን ከማፋጠን እና ከመድግፍ ወጪ ህዝብን በህዝብ ላይ የሚያስነሳ፣ ዜጎችን የሚያፍናቅል ፕሮፓጋንዳና የግልጽም የድብቅ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከማድርግ እንዲቆጠቡ ማድርግ፡፤ ያደርጉትንም በህግ መጠየቅ።

9. ባልፉት 27 አመታት ለደረሱ በደሎች ህግ-ወጥ ስራዎች ምንም እንኳ ወያኔ የአንበሳውን ድርሻ ቢይዝም አብርው ሁነው በህዝብ ላይ ሰቆቃና በደል ያድርሱ የነበሩ የኢህአዴግ ና ተባባሪዎቻቸው የሆኑ ሌሎች ፓርቲ ካድሬ እንዲሁም ባለስልጣኖችን በእኩል ለፍርድ ማቅረብ። በትግርይ ያሉ ወድንሞቻችን ሀገር ውስጥ የሚድርገው ለውጥ የነርሱም እንዲሆነ የሚያስችልን ስራ መስራትና በሽግግሩ ሂድት ላይ በዋና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድርግ።

10. በመንግስት ሃላፊነት የተቀመጡ መሪዎች የሚሰጧቸው አዲስ የሽግግር ግዜ ሹመቶች በጎሳ ወይም በጥቅም ወይም ድብቅ የፖለቲካ አላማ ለማራመጃ እንዳይሆን፤ በብቃትና ለህዝብ በሚጠቅም መልክ መሆን አለበት። ይህንንም ያለው ፓርላማ አባላት በብቃት ይከታትሉት ለማለት ቢያስችግርም (የህዝቡ እውንትኛ ተውካይነታቸው በነጻ ምርጫ ስላልተመርጡ) ገለልትኛ የአገር ሽምግሌዎች ቢመረምሩት። ሚዲያውም ይህንን እያጋለጠ ጥፋትን አስቀድሞ ማስቆም የሚቻልበትን መንግድ ማስያዝ ግዲታ አለበት።

11. ለዲሞክራሲ መሰርታዊ ቅድም ሁኒታዎች የሆኑትን የመንግስት መዋቅሮች እንደ ነጻ የፍርድ ቤትን፣ ፖሊስ፣ መከላከያ ሃይል፣ የጸጥታ ሲኩሪት መዋቅርን፣ ሚዲያን፣ የሰአባዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን (እንባ ጠባቂ ተቋሞችን) የምርጫ ኮሚሽን በነጻነትና በገለልትኛ እንዲዋቀር፤ ላለው መንግስት መሳርያ ሳይሆን ለተመርጠ መንግስት ሁሉ የሚታዘዝ ተቋም እንዲሆኑ ማድርገ ። ይህም በብቃትና በችሎታ በትምህርትና ልምድ ላይ የተመስርተ እንጂ በፖለቲካ አመልካክት ደጋፊንት መሰረት ላይ እንዳይሆን ብርቱ ስራ መስራት። ሚዲያውም ይህን እያረጋገጠ መዘገብ።

12. ሀገራዊ መግባብትና የህዝብ እርቅ ሳይፈጸም እንዲሁም በህግ ህዝብንና አገርን የሚበትን አንዱን በአንዱ ላይ የሚያስንሳ የሚያጋጭ ዘምቻን ሳይገደብ ለምርጫ ሩጫ እንዳይድርግ።

13. አሁን አገር በመምራት በመንግስት መንበር ላይ ያሉ ሃላፊዎች በህዝብ ምርጫ ስልጣኑን የያዙ አለመሆናቸውን አወቀው ነገር ግን "የለውጥ ፈላጊ" የቀድመው ስርአት አካል መሆናቸውን ና ለህዝብ በሰጡት ተስፋ የተቀብላቸው መሆኑን አውቀው፤ 27 አመታት ሙሉ የተደርገውን የህዝብ ትግል ዘላቂ፣ ሰላምዊ ዲሞክራስያዊ የህዝብ አንደንት ያሉብት አገርን ለመምስርት ለሽግግር ግዜ ብቻ እንዲያገለግሉ በከፍትኛ ሀገራዊና የህዝብ አደራ እንዲመሩ፤ ላድርጉትም ለሚያደርጉትም መልካም ስራ ህዝቡና ታሪክ የሚያመስግንቸው ሲሆን ለሚሰሩት ባለማወቅ ስህተት ህዝቡን ይቅርታ እየጠየቁ ለሚውስዱት ውሳኔም እንዲሁም ማድርግ የነበርባቸው ግን ሳይወስኑ ለሚቀሩ ወሳኝ ጉዳዮች (conscious omission) እንዲሁም ጥፋት ሃላፊነቱንና ተጠያቂነትን መቀበል ይኖርባቸዋል። የሚወስኑትን እያንዳንዱ ወሳኝ ውስኔ "ይሄ ነገር አገር ና ህዝብ ይጠቅማል? የህዝብ አንድነትን መግባብትን ያጠናክራል? ለተገፉና ለተርሱ ወገኖችን ችግር ለመቅርፍ ያግዛል? ፍታህዊና ሞራላውንት አለው?" ብለው ሁሌም ራሳቸውን እንዲጠይቁ ይገባል።

የዚህ የሽግግር ግዜ ውጤቱ ለ50 አመታት የተደከምትን የህዝብ ትግል እውን ማድርጊያ፤ በዜግንት እኩሉነት፣ በህዝብ መቀራርብ ህብረት ላይ፣ ዲሞክራሲ የሰፈንባት፣ ሃይልኛች የማይፈንጩባት፣ ስልጣን በሰላምና በህዝብ ምርጫ የሚያዝበት፣ ድሃ የማይበደልባት ስልጣን ለህዝብ ቅርብ የሆነበትን የመንግስት ስርአት ለማምጣት ሁላችንም ይህን የሽግግር ግዜ እውን እንዲሆን ማገዝ ያለብን ሲሆን ሙሉ አደራውን

ለእህት-ውንድሞቻችን ብቻ ሰጠተን እንርሱን መውቅስ ሳይሆን፤ ዋናው አላማ እንዲሳክ  በሙተባበር ችግሩን ሰላማዊ በሆነ በመነጋገር እይፈታን የህዝቡን ራእይ እውን ለማደርግና አግርችንን ታላቅ አገር ለማድርግ አግዚሓቤር አምላክ ይርዳን።